# ጸቡ ከመምህሩ ወይስ ከማሕበሩ?

የሃገሬ ሰው በሕብረተሰቡ ተቀባይነት የሌለው ሥራ ሲሰራ ሲያይ በመገረም ድምፁን ከፍ አድርጎ ይህን ይላል፤

‘እዩት ጀግና ሲፋፉ፤
ሱሬው ቀዶ ሱሬ ሲሰፋ! ‘

የወያኔ\ ኢ ሕ አ ዴ ግ መንግሥት ለአሥራ ሰባት ዓመት ሱሬውን ቀዶ ሱሬውን ሲሰፍ በጋሕድ እያሣየን ነው።
ለምሳሌ በአንድነት የኖረን ሕዝብ በዘር ከፍሎ፤ በክልል ወስኖ፤ አስተዳደር ሲመሰርት ፤ አቡን ሽሮ አቡን ሲቀባ ፤ ኢማም አውርዶ ኢማም ሲሾም፤ የሠራተኛ ማሕበር አፍርሶ፡ የአፍቃሪ ዘር ማሕበር ሲያቋቁም፤ ሐቅን የሚያቀርብ፡ የጋዜጠኛ ማሕበር አፍርሶ፡ በሆድ አደር ጋዜጠኛ ማሕበር ሲተካ፤ የሱሬ ቀዶ ሱሬ መስፋቱ ሥራ ቀጥሎ ሰሞኑን በአንጋፋው ከስልሣ ዓመታት በላይ ባስቆጠረው በኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር ላይ አርፏል።
ይህ የሞያ ማሕበር ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም መምህራን ማሕበር አባል ነበር። በዚያ ምክንያት የመማር ማስተማሩን ተግባር ለመጋራት ከዓለም ዙሪያ መምህራን የነፃ ትምህርት አገልግሎት ለመስጠት ከሐዜ ኃይለሥላሴ ዘመን ጀምሮ ወደ ሃገራችን ሲመጡ ቆይተዋል። ይህ ዛሬ በፍርድ ገምድል ዳኞች ግባ ተመሬት የተፈጸመበት ማሕበር በሥልጣን ላይ ላሉት ሳይቀር አገልግሎት ሰጥቷል። የፍርዱም ውሳኔ ያሣዘነው ለአሥራ አምስት ዓመት በፍርድ ቤት የተጉላሉትን የሥራ አስካጅ ኮሚቴውና ዋና ጸሐፊውን ጉመራው ካሣን ብቻ ሳይሆን በሞያው የተሰማሩትን በዓለም ዙሪያ ያሉትን መምህራን ጭምር ነው። ለዚህም ነው ጸቡ ከመምህራኑ ወይስ ከማሕበሩ ብዬ ጥያቄ ያቀረብኩት።
ይህ የሞያ ማሕበር የመማር ማስተማሩን ሥራ ያለምንም ጣልቃ ገብነት ከስልሳ ዓመታት በላይ በመላው የኢትዮጵያ ግዛቶች ሲያከናውን ቆይቷል።
ሐዜ ኃይለሥላሴ ይህን የሞያ ማሕበር ለመማር ማስተማሩ ሥራ ቁልፍ መሆኑን አምነውበት እንዲመሰረት ሲፈቅዱ በማሕበሩም የውስጥ ሥራ ላይ ምንም ዓይነት ተጽኖ አልነበራቸውም። ያም በመሆኑ የዕውቀት አባት በመባል ሲታወሱ ይኖራሉ።
መምህራንም መሉ መብታቸውን ተጠቅመው የማሕበሩን መሪዎች መርጠው ከማስተማር መማሩ ሥራ በተጨማሪ በሕብረተሰቡ ውስጥ በወላጅ ኮሚቴ ፣ በገጠር አስተዳደር ጉበኤ በጎልማሶች ትምህርት በሚተፍ የሞያ ግዴታቸ ውን ተወጥተዋል።
በዲሞክራሲ የተመረጡት የመምህራን ማሕበሩ መሪዎቹም ብቃትና ጥንካሬቸውን በሕብረተሰቡ ውስጥ አስመስክረዋል።
( I am proud to be a teacher) ‘በአስተማሪነቴ እኮራለሁ ‘ የሚለውን መፈክራቸውን አንግበው የዕውቀትን ዘር ሊዘሩ፡ ድንቁርናን፡ ሊያጠፉ፡ የበታችነትን ስሜት ሊያስወግዱ፡እኩልነትን ሊሰብኩ፡የዘር ፖለቲካን ሊያመክኑ፡የጠባብነትን አዙሪት ሊያከሽፉ ሲሰማሩ ይህ ማሕበር ደጀናቸው ነበር።
የሞያው ማሕበርና መምህራን እጅና ጓንት ሆነው ሲሰሩ በሕብረተሰቡ ውስጥ የነበራቸው ተቀባይነትና አክብሮት የላቀ ነበር። አንዳንድ የገጠር አካባቢዎች የሕብረተሰቡ አባሎች እርስ በርስ ችግር ሲገጥማቸው ፍርድ ቤት ወይም ፖሊስ ጣበያ ጉዳያቸውን እንዲፈቱላቸው ከመሄድ ትምህርት ቤትን መርጠው ከመምህራን ዘንድ መፍትሔ ለመሻት ይመጡ ነበር።

ሁሉም ነገር እንደነበር አይቀይምና የሐፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ ንግሥ አክትሞ በወታደራዊ መንግሥት ሲተካ የመማር ማስተማሩ ሥራ እጅጉን ተጎዳ። መምህራንም የሞያ ማሕበራቸውን መከታ አድርገው ለትምህርቱ ጥራት በቆራጥነት ቆሙ። በዚህም ምክንያት ደርግ ማሕበሩን እንደ አንድ ተቃዋሚ የፓለቲካ ደርጅት አድርጎ ወሰደው። በመሆኑም በመምህራን ላይ ክትትሉ ን አጠናከረ።
ለምሳሌ በ1969 ዓም በጅማ ከተማ በተደረገው የማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ፡ ደርግ በሰብሰባው አዳራሽ ውስጥ ድምፅን የሚቀዳ መሣሪያ በማስገባት የስብሰባውን ክንውን በቴብ ቀድቶ ለሃገራቸው ራዕይ የነበራቸውን መምህራን የርሱን የፓለቲካ መስመር ባለማስተጋባታቸው ማሳደዱን ቀጠለ። ታዋቂ መምህራን ከእስራት እሰከ ግድይ እርምጃ ተወሰደባቸው።የወቅቱ የጅማው መምህራን ማሕበር ዋና ጸሐፊ የነበረው ክበበም የተገደለው በተገኘው የስለላ ማስረጃ ነበር።
ጎመራው ካሣ የደርግ መንግሥት ለኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር ፡ ለመማርና ማስተማሩ ሥራ ባጠቃላይ ተስፋ ሰጪ አለመሆኑን አስቀድሞ የተገነዘቦ፣ ሞያው ግድ የሚለውን ለቤተሰብ ለተማሪዎቹ ለሕብረተሰቡ በሐቀኛነት ማሕበሩን ጋሻ አድርጎ ቆሟል። ግርፍና እስራት ደርሶበታል። ዛሬ በጉታና ሞ ቤዬ በአሸባሪዎች ላይ የሚወሰደው ዓይነት በውኃ ሰውን የሚያሰቃዩበት መሣሪያ የተፈተሸበት መምህር ቢኖር ጎመራው ካሣ ነው።ከዚያም በኋላ ከሞት ተርፎ በእስር ቤት ሆኖ በሸማኔነት ሥራ ተሠማርቶ እንደ እርሱ በሞያቸው ጸንተው በገጠር ያለክፍያ ተሰማርተው ለነበሩ መምህራንም እርዳታውን ሲቸር ቆይቷል።
ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ሆነና እንጂ በአሁኑ ወቅት የመማሩና የማስተማሩን ተግባር ግባ ተመሬቱን ያጣደፉት አቶ አዲሱ ለገሠና በረከት ስመኦን የዚህ ማሕበር አባል ነበሩ። እነርሱ ብረት ሲመርጡ የመምህር ጎመራው ካሣ ምርጫ ጠመኔና መጽሐፍ ነበር።
በዛሬው ቀን የማሕበሩ ግባ ተመሬት አዲሱና በረከት አባል በሆኑበት መንግሥት ሲፈጸም የተመለከተው ጎመራው የቱን ያህል በቆጨው? ከዚህ ማሕበርና ከመምህርነት ሞያ ጋር በመንፈስ በአካል ከተሳሰሩ ይሄው ሰላሳ ስድስት ዓመታቸው። ከሰላሳ ስድስት ዓመት በፊት ከመምህራን ማሰልጠኛ ተመርቆ ከሱማሌ ወሰን ሲመደብ የሚያስተምራቸውን ልጆች ለማየት ከመጓጓት ሌላ እንደ አንዳንድ መምህራን በከተማ ለመመደብ አልቃጣም።የፖሊስ ቀለብ አመላላሽ በሆነ መኪና ላይ ከጆኒያ ጋር ተጭኖ ከአካባቢው ሲደርስ ያገኛቸው ተማሪዎች የጉራ፡ የሱማሌ፡የራይቱ የኦሮሞ ዝርያዎች ነበሩ።
ስለጎመራው ካሣ የዚችን ያህል ለመከተብ የፈለኩት ለአለፉት ዘመናት ከጣሊያን ድል በኋላም እንደሚነገረው ብዙ ጊዜ መሰዋዕትነት የከፈሉ ግለሰቦች ለሃገራቸው የከፈሉት ወረታ ገኖ አይነገርም። ባህል ሆኖ መልካም አድራጊዎች ስለራሳቸው ቀርበው አይገልጹም።የድል አጥቢያ አርበኞች መድረኩን ይቆጣጠሩትና ሐቀኞቹን በአካባቢው ዝር እንዳይሉ ያደርጓቸዋል። አሁንም የመምህራኑን ማሕበር ለመቆጣጠር የሚሽቀዳደሙት ይህን መሰል ሰዎች ናቸው ። የመናገርና የመፃፍ መብት ቢኖር ኖሮ በእንደዚህን አካባቢ ዝር አይሉም ነበር። ሃገራችን ወደፊት እንዳትራመድ ከሚመጡት አምባገነኖች ጋር እያበሩ መቀመቅ ይዘውን የሚወርዱት እነዚህ መሰል ከቤተሰብ ከትምህርት ቤት ከሕብረተሰቡ ምንም ያልተማሩ ግለሰቦች ናቸው።
ይህ ሁኔታ በሕብረተሰባችን ውስጥ ሕዝብን ባሳተፉ ሥፍራዎች ሁሉ ጎልቶ ይታያል። በአንድ ወቅት በአሜሪካን አንድ ከተማ ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተሠርቶ ሲመረቅ የእህቴ ልጅ ጋብዞኝ ተገኝቼ ነበር። እናቶችና መዘምራን ወደተቀመጡበት አመልክቶኝ ይህን ቤተክርስቲያን የሠሩት እነዚያ ናቸው ብሎ

ነገረኝ። ከመግቢያ በር አካባቢ ነበር የተቀመጡት ወጣቶቹ በማዲያት የተለበለበ እርፍ ይመስላሉ እናቶችም የተጉሣቆሉ ነበሩ።ከሡገነቱ አካባቢ ነጭ በነጭ ለብሰው ከአባ ደርበው እንቧይ የመሳሰሉ ዱብ ዱብ የሚሉት ቤተክርስቲያኑ ሊጠናቀቅ ሲል ብቅ ያሉ ናቸው ብሎ አጫውቶኛል። ሌላው ደግሞ ነጮች እንደሚሉት (human touch) ለጹሑፌ ሕይወት ለመስጠት ነው። በሁሉም መስመር በተለይ በመማርና ማስተማሩ መስክ በግልጽ መናገርና መጽሐፍ ባህላችን እንዲሆን ፈቅደን ቢሆን ፤ የኤሊን ታህል ፍጥነት በተጓዝን ነበር።

ወያኔም ቀስ በቀስ ምልምሎችን አዘጋጅቶ የቆየውን የመማርና የማስተማሩ ሥራ መዐከል ያደረገውን የሞያ ማሕበር በፍርደ ገምድል ዳኞቹ ግባ ከመሬቱን አያስፈጽምም።

የቀድሞውን የማሕበሩን ዋና ጸሐፊ የነበረውን አሰፋ ማሩን በጠራራ ፀሐይ አያስገድልም። የኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር ፕሬዘዳንት የነበሩት ዶክተር ታዬ ወልደሰማያትም በዘር ላይ የተመሠረተ የሞያ ማሕበር ለመማር ማስተማሩ ሥራ ሆነ ሰሃገሪቱ ዕድገት ጠንቅ መሆኑን በመጠቆማቸው ለስድስተ ዓመት ጽኑ እስራት አይደርስባቸውም ነበር።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የመማር ማስተማሩ ሥራ አለመካሄዱ የመላው የሃገሪቱ ጉዳይ እንጅ የመምህራን ወይም የማሕበሩ ተመራጮች አልፎም የተቃዋሚ ፓለቲካ ፓርቲ አባላት ብቻ አይደለም። ትምህርት ቤቶች በታንክና በወታደር ተከበው ቢሻቸው ክፍል ገበተው ሲገድሉ መምህሩን ሲያስፈራሩ ያየ ተማሪ ምን አይነት ዜጋ ይወጣዋል? አንዳንድ የዋሆች የትምህርቱን ጥራትና የመምህራኑን ብቃት ከስሌት ሳያስገቡ የትምህር ቤቶችን ብዛትና የተማሪዎቹን ቁጥር በማየት ብቻ የመማር ማስተማሩ ሥራ የሚካሄድ የሚመስላቸው አሉ። የግል ትምህርት ቤቶች በብዛት መከፈታቸው ዕውቀትን ለማስፋፋት ሳይሆን ገንዘብ ለመሰብሰብ ነው። ሌሎቹም ደግሞ በጣም ብዙ ገንዘብ ለትምህርት በማውጣታቸው ወይም ውጭ አገር ልጆቻቸውን ልከው በማስተማራቸው ያላቸውን ራዕይ ከግብ ያደረሱ የሚመስላቸውም አልጠፉም። ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የሚኖረው ባለሞያ መክሮበት በጥናት ተደግፎ በየደረጃው ተመሳሳይ የሆነ ሥረዓተ ትምህርት ካልተቀረጸ በዚህ ይዘት ከየትም አንደርሰም። እዚህ ላይ አንባቢዬ እንዲረዳልኝ የምሻው ጭራስ እንቅስቃሴው ይቁም ማለቴ አይደለም። እንደውም አፍራሽን መቋቋም የሚቻለው ከርሱ ተሽሎ በመገኘት ነው። በኦሮመኛ እንዲህ ይተረታል ‘ አፋን ጉዶ ሐርካን ጢቆ ‘ በአማርኛ ‘ እቤት ሥሩ ሥሩ ማአገር ላይዙ ‘ ይባላል። ስለሃገራችን ጥፋት ሁሌ ከማውራት በተግባር የሚገለጽ ሥራ ከያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል።

ለምሳሌ በውጭ አገር ከሃምሳ ሺ በላይ ኢትዮጵያውያ መምህራን በስደት እንደሚገኙ ይነገራል። በወር አስር ብር ብናዋጣ በየወሩ ቢያንስ አንድ ትምህርት ቤት እንሰራለን። የወያኔ\ኢሕአዴግ እንደሆነ አጥፍቶ ለመጥፋት የተዘጋጀ መንግሥት ነው። በአንድ አገር ትምህርት በወጉ ካልተሰጠ የሃገሪቷ ዕድገት ከጥያቄ ውስጥ ይገባል።

ያም ሆነ ይህ የዚህ መንግሥት ጸቡ ከመምህራኑ ወይም ከማሕበሩ ብቻ አይደለም በአጠቃላይ ከሃገሪቱ ሕዝብ ጋር ነው።

ታደለ መኩሪያ